# አብዮታዊት ኢትዮጵያ

6

★ የኢትዮጵያ አብዮት ከቺሊ የሚማረው

★ ዘመቻው በወዝ አደሩ ዓይን

★ የቦልሼቪክ ፓርቲ አጭር ታሪክ

★ የምርምር መሠረታዊ ስልቶችና ሁለቱ ተቃራኒ መልሶች

ሐምሌ ፲፩ - ፲፱፻፸፯ ዓ.ም.

**ለውይይት መነሻ**

አብዮታዊት ኢትዮጵያ ከቊጥር ፬ ጀምራ «ለንማርክስ ፍልስፍና አጭር መግቢያ» በሚል ርእስ ሥር ተከታታይ ትምህርታዊ የሆኑ የፍልስፍና ጽሑፎች ታቀርባለች ። እነዚህ ጽሑፎች የማርክሲዝምን ርእዮተ ዓለም ገና ለመጀመሪያ ጊዜ ለሚተዋወቁ የውይይት ክበቦች መነሻ ሃሳቦች እንደሚሰጡ ሆነው የቀረቡ ናቸው ።

# የምርምር መሠረታዊ ስልቶችና ሁለቱ ተቃራኒ መልኮች

፪ኛ ትምህርት—ከን· ዓ·

አንድ የተወሰነ ዓላማ ለመድረስ የምንጠቀም በት መንገድ አለ ። የተሳሳተና የማያዋጣ መንገድ ከያዝን ዓላማችን አንደርስም ። ትክክለኛ ስልት ከተከተልን ግን ዓላማችንን እንመታለን ። የዚህ « የስልት» ጉዳይ ለማንኛውም ነገር አስፈላጊ ቢሆንም ፤ የአንድን ነገር እርግጠኛ ሁኔታ አጣ ርቶ ለማወቅ ምርምራችን የሚከተለውን ስልት ጠጋ ብሎ መመልከት ያስፈልጋል ።

ፍልስፍና ስለዓለም ፤ ስለአካባቢያችን ሁሉ አጠቃላይ የሆኑ አንዳንድ ሐቆችን ተመራምሮ ለማግኘት የሚደረግ ምርምር ነው ብለናል ። ስለ ዚህ ይህንን አጠቃላይ ምርምር ለማድረግ አጠቃ ላይ የሆነ የምርምር ዘዴ ፤ ሁለገብ የሆነ የጥናት ስልት ያስፈልጋል ።

ይህ አጠቃላይ የምርምር ስልት እንደ ፍል ስፍና እምነታችን ይስፋፋል ። ለምሳሌ ዓለም አንድ ጊዜ « እንደተፈጠረች » ቆማ የቀረችና ቆማ የምትቀር ነገር አድርጐ የሚመለከት ሰው ፤ ዓለ ምን በሚያጠናበት ጊዜ የምርምር ስልቱ እንቅ ስቃሴዋ ላይ አያተኩርም ። አንድ ነገር ለዘለዓ ለም የነበረ ለዘዓለም የሚኖር ነው ከተባለ አሁ ንም ዱሮም ፤ ወደፊትም ያው ነውና የምርምር ስልቱ ስለታሪኩና ስለአመጣጡ ግድ የለውም ። ወደፊትስ ምን ይሆናል የሚለው ምርምር ውስጥ እስከዚህም አይገባም ። አካባቢያችን በማያቋርጥ እንቅስቃሴ ላይ ነው የሚል ከሆነ ግን ይህ አጠ ቃላይና በሁሉም ነገር ያለ የማያቋርጥ እንቅስቃሴ የሚከተላቸውን አጠቃላይ የእንቅስቃሴ ሕጎች ለማወቅና ማንኛውንም ነገር በነሱው እንኖር ለማ ጥናት ይፈለጋል ።

ባጭሩ የምርምር ስልታችን ራሱ ስለቁስ አካል ካለን እምነት ጋር የተያያዘ ነው ማለት ነው ። እንግዲህ እነዚህን ሁለት ተቃራኒ የምርምር ስልቶች ጠጋ ብለን እንመልከታቸው ።

የማርክሲዝም የምርምር ስልት ዲያሌክቲ ክስ የተባለው ነው ። ይህ የምርምር ስልት «ሜታ ፊዚክስ » ከተባለው የምርምር ስልት የተለየና እን ዲያውም የሱ ተቃራኒ ነው ። የዲያሌክቲክስን የምርምር ስልት ዋና ዋና ሕግጋት ከሜታፊዚ ክስ ጋር እያነፃጸርን እንመልከት ።

## የዳያሌክቲካዊ ለውጥ ሕግ ወይም « ሁሉም ያልፋል እስኪያልፍ ያለፋል »

ሜታፊዚክስ የተባለው የምርምር ስልት ከእ ንቅስቃሴ ርጋታን ይመርጣል ። « ዓለም ምንጊ ዜም ያው ነች ። ሰው ምንጊዜም ሰው ነው አይ ቀየርም ። ከፀሐይ በታች አዲስ ነገር የለም» ይላል ። የዲያሌክቲክስ የምርምር ስልት ግን ከመነሻው « አካባቢያችን በማያቋርጥና ዘለዓለማዊ በሆነ እን ቅስቃሴ ላይ ነው » ብሎ ያምናል ። ኤንግልስ እን ዳለው « የትም ቢሆን ፤ ምንጊዜም ቢሆን ቁስ አካል ያለእንቅስቃሴ ኖሮ አያውቅም ። ወደፊትም አይኖርም ። »

ስለሆነም የዲያሌክቲክስ የምርምር ስልት ማንኛውም ነገር ፤ ከትንሿ አቧራ አንሥቶ እስከ ከዋክብት ድረስ ፤ በዓለም ላይ ያለ ነገር ሁሉ

ዓለም ራሷም ብትሆን በማያቋርጥ እንቅስቃሴ ላይ ነች ይላል ። ማንም ሰው ቢሆን ሁለት ጊዜ አንድ ወንዝ ውስጥ አይዋኝም ። ተመልሶ ለመዋኘት በሚገባበት ጊዜ ውሀውም ፈሳሽ ነውና ተለውጧል ። ሰውዬውም በየሴኮንዱ በውስጡ ብዙ ሕዋሳት ስለሚሞቱና ስለሚወለዱ ያ የቀድሞው ሰው አይደለም ።

ስለዚህ በሜታፊዚክስ የምርምር ስልት የሚጠቀም ሰው ማንኛውንም ነገር ሲያጠና እንደ ቆመ ነገር ተመልክቶ ያጠናዋል ። በዲያሌክቲክስ የምርምር ስልት የሚጠቀም ሰው ግን አንድን ነገር ሲያጠና በእንቅስቃሴው ላይ ነው የሚያተኩረው ። የሚያጠናውም እንቅስቃሴውን ነው ።

ነገር ግን በዲያሌክቲክስ አስተሳሰብ « ማንኛውም ነገር በማያቋርጥና ዘለዓለማዊ በሆነ እንቅስቃሴ ላይ ነው » ማለቱ ብቻ አይበቃም ። ሁሉ ነገር የተያያዘ ነው ይላል ። ዓለም ዩኒቨርስ «ተፈጥሮ » ኅብረተሰብ ፤ ግለሰብ . . . . በጠቅላላው ተሳስረውና ተቀነባብረው የሚንቀሳቀሱ ነገሮች ናቸው። እያንዳንዱ ነገር የሌሎች ነገሮች ተፅዕኖ አለበት፤ እያንዳንዱ ነገር መልሶ በሌሎች ነገሮች ላይ ተፅዕኖ ያደርጋል ። በሜታፊዚክስ የምርምር ስልት የሚጠቀም ሰው ግን ሁሉንም ነገር ለብቻው ነጥሎ ይመለከታል ። ፈረስ ፈረስ ነው ። ላም ላም ነች ። በእንስሳት ዓለም ውስጥ ፈረስና ላም የተያያዙበት ብዙ ነገር እንዳለ አይመለከትም ። ፖለቲከኛ ፖለቲከኛ ነው ። ፈላስፋ ፈላስፋ ነው ። ሐኪም ሐኪም ነው ስለሚል በኅብረተሰቡ ውስጥ እነዚህ ሁሉ የተያያዙና አንዱ በአንዱ ላይ ተፅዕኖ እንደሚያደርግ አይገነዘብም ። ስለዚህ ሲያጠናና ሲመራመር አንዱን ከአንዱ ጨርሶ ለያይቶ ነው ። በተጨማሪ በሜታፊዚክስ የምርምር ስልት የሚጠቀም ሰው በእንቅስቃሴና ባለውጥ ስለማያምን በነዚህ ነገሮች መሐከል ያለው ልዩነት ዘለዓለማዊና ጨርሶ የማይበገር ማንም ሊወጣው የማይችለው ልዩነት አድርጎ ያቀርበዋል ።

እንግዲህ በዲያሌክቲክስ ሕግ ጠቅላላው አካባቢያችን የተያያዘና የተቀነባበረ ከመሆኑ በላይ ተያይዞ የሚነጉድና የሚንቀሳቀስ ነው ማለት ነው ። በሀገራችን ለዚህ ተስማሚ የሚመስለን ተረት « ሁሉም ያልፋል እስኪያልፍ ያለፋል » የሚለው ነው ። ዲያሌክቲክስ እንግዲህ ሌላ ምንም ነገር ሳይሆን ሁሉም ያልፋል ካለ በኋላ እነዚህ የተሰበጣጠሩ ነገሮች በሙሉ ለምን እንደሚያልፉ እንዴት እንደሚያልፉና ወዴት እንደሚያልፉ የሚጠቁምና የእንቅስቃሴን አጠቃላይ ሕግጋት የሚያበሥር ሕግ ነው ።

« ሁሉም ያልፋል » የሚለው ማንኛውም ነገር በማያቋርጥ እንቅስቃሴ ላይ መሆኑን የሚያበሥር አጠቃላይ ሕግ ነው ። ጥያቄውም እንግዲህ ለዚህ አጠቃላይ እንቅስቃሴ አጠቃላይ የሆነ ምክንያት አለወይ ? የሚለው ነው ። ማርክሲዝም ለዚህ አዎን ብሎ ይመልሳል ። የማንኛውምንም እንቅስቃሴ ምንጭና አንቀሳቃሽ ኃይል <u>የተቃራኒዎች ተዋሕዶና ትግል</u> ( ዩኒቲ ኤንድ ስትራግል ኦፍ ኦፖዚትስ ) በሚለው የዲያሌክቲክስ ሕግ ያስረዳል ።

«ሁሉም ያልፋል» የሚለው በማንኛውም ነገር ያለ አጠቃላይ ሕግ ከሆነ ይህ እንቅስቃሴ <u>እንዴት</u> እንደሚካሔድ ሂደቱን የሚያመለክት አጠቃላይ የሆነ ሕግ አለ ወይ ? አዎን ማርክሲዝም ሁሉ ነገር ሲንቀሳቀስ የሚከተለውን <u>አጠቃላይ</u> ሂደት ለማመልከት <u>ከብዛት ወደ ዓይነት</u> መለወጥ (ቼንጅ ኦፍ ኳንቲቲ ኢንቱኳሊቲ) በሚለው የዲያሌክቲክስ ሌላ ሕግ ይጠቀማል ።

«ሁሉም ያልፋል» በሚባልበት ጊዜ ማንኛውም ነገር ሲለዋወጥ በአንድ በተወሰነና በታወቀ አጠቃላይ አቅጣጫ ነው ወይስ አንዱ ወደ አራንባ ሌላው ወደቆቦ ? አንዱ ወደታች ሌላው ወደላይ ? ማርክሲዝም ይህንን አጠቃላይ አቅጣጫ ለማሳየት <u>የሻሪ ሽርት</u> (ኔጌሽን ኦፍ ዘ ኔጌሽን) በተባለው ሦስተኛ ሕግ ይጠቀማል ።

እስቲ እንግዲህ እነዚህን አጠቃላይ የለውጥ ሕግጋት ጠጋ ብለን እንመልከት ።



## ፩ኛ ፤ የተቃራኒዎች ተዋሕዶና ትግል

ፀረ—ሳይንስ ወይም በሜታፊዚክስ የሚያስብ ሰው ሁለት ተቃራኒ ነገሮች ሲገናኙበት ይሸበራል ። ቅጡ ይጠፋዋል ። ሞት ካለ ሕይወት የለም። አንድ ሰው ከኖረ ኖረ ከሞተ ሞተ እንጂ በአንድ ጊዜ ይሞታል ይኖራልም ማለት አይችልም ይላል ።

በዲያሌክቲክስ ዘዴ የሚያስብ ሰው ግን ጭራሹን ይግረምህ ይልና ነገሩን እስከነጭራሹ በመገልበጥ ማንኛውም ነገር እንዲኖር ከተፈለገ ተቃራኒውም መኖር አለበት ። ሁሉም ነገር የተቃራኒ ነገሮች ኅብረት ወይም ተዋህዶ ነው ይላሉ ። ስለሞትና ሕይወት ብንሔድ ለምሳሌ ሳይንስ አበጥሮ እንደሚያስረዳው በየሴኮንዱ በአንድ ሰው አካል ውስጥ የሚወለዱ የሚያድጉ የሚሞቱ ሕዋሳት አሉ ። የአንዳንዶች ሕዋሳት መሞት የሌሎቹ ደግሞ መወለድና ማደግ በአንድ ላይ የሚካሔድ ጉዳይ ነው ። የሚሞቱ ከሌሉ የሚወለዱትም አይኖሩም ። ሞት ከሌለ ሕይወት የለም ። ጨለማ ከሌለ ብርሃንም የለም ። ጢሰኛ ከሌለ ባለርስት ሊኖር አይችልም ። በዝባዥ ከሌለ ተበዝባዥ የለም ይላል ።

በሌኒን አነጋገር ከዲያሌክቲክስ አጠቃላይ የለውጥ ሕጎች እንደዋና ሕግ መቆጠር ያለበት ይኸ ሕግ ነው ። መላ «ተፈጥሮ » መላ ቁስ አካል በማያቋርጥ እንቅስቃሴ ላይ ነው ካልን ዘንድ የዚህ ሁሉ እንቅስቃሴ ምንጭ ምን እንደሆነ የሚያስረዳው ሕግ እውነትም መሠረታዊ ሕግ መባል ይገባዋል ።

ይህ ሕግ የማንኛውንም እንቅስቃሴ ማለትም በጠቅላላው ዓለምን ኅብረተሰብን ፤ ግለሰብን እንዲንቀሳቀሱ የሚገፋፋ ምንጭ ነው ሲባል እንዴት ነው ?

<u>ማንኛውም ነገር ተቃራኒ ነገሮች ተዋህደው ይገኙበታል</u> ። ይህ የመጀመሪያው የዲያሌክቲክስ ሕግ አንዱ አካል ነው ። እነዚህ ተቃራኒዎች ተቻችለው በፍቅር የሚቀመጡ አይደሉም ። በመካከላቸው የማያቋርጥ ትግል አለ ። የማንኛውም ለውጥ መወለድና መሞት የዚህ የተቃራኔዎች ትግል ውጤት ነው ።

ከላይ ወዳነሳነው ተረት ብንመለስ ሁሉም ያልፋል ብቻ ሳይሆን የሚያልፈው በትግል እንደሆነ እናያለን ። ለዚህ ነው <u>«እስኪያልፍ ያለፋል»</u> የሚባለው ።

የቅራኔዎች ተዋህዶና ትግል ሲባል ግን መጠንቀቅ ያስፈልጋል ። ማንኛውም ነገር በውስጡ ቅራኔዎችን አዝሏል ሲባል በአንድ በተወሰነ ጊዜ የሚይዛቸው ቅራኔዎች የተለያዩ ሲሆኑ ዋና ዋናዎቹ ግን በሦስት ዓይነት ሊጠቃለሉ ይችላሉ ።

<u>ውስጣዊና የውጭ ተቃርኖ</u> ። ውስጣዊ ተቃርኖ በአንድ በተወሰነ ነገር ውስጥ ያለ ቅራኔ ነው ። የውጪ ቅራኔ ደግሞ ይኸው ነገር በአካባቢው ካሉት ሌሎች ነገሮች ጋር የሚያጋጥመው ቅራኔ ነው ። ዋናው አንቀሳቃሽ ቅራኔ <u>የውስጡ</u> ቅራኔ ነው ። የውጭ ቅራኔ ለውጥን ፤ እንቅስቃሴን ለጊዜው ሊገታ ፤ ሊያፋጥን ፤ ይችላል ። ግን ከዚህ አልፎ የሚሔድ ሚና የለውም ።

<u>ተጻራሪና ተቻቻይ ቅራኔዎች</u> ። ይህ የአጥፊና ጠፊ ቅራኔ ነው ። ተጻራሪ ቅራኔ በምንም ዓይነት ሊታረቁ በማይቻሉ ፤ አንዱ ሌላውን እስኪያጠፋ ድረስ ትንንቅ የማይለይበት ቅራኔ ነው ። ለምሳሌ በባለርስትና በጢሰኛ መሀከል ያለው ቅራኔ እንደዚህ ነው ። የአጥፊና ጠፊ ቅራኔ ነው ። ሊፈታ የሚቻለው በኅብረተሰብ ሹም ሽር ወይም በአብዮት ብቻ ነው ። ተቻቻይ ሲሆኑ ግን በመሠረቱ የጋራ ጥቅማቸው የሚያገናኛቸው ግን ደግሞ ጥቅማቸው ሙሉ በሙሉ አንድ ያልሆነ ወገኖች መሀከል ያለ ቅራኔ ነው ። ለምሳሌ በአርሶ አደርና በወዝአደር መሀከል ያሉት አንዳንድ ቅራኔዎች ተቻቻይ ቅራኔዎች ናቸው ።

<u>ዋናና መለስተኛ ቅራኔዎች</u> ። አንድ ነገር በውስጡ የሚይዛቸው ቅራኔዎችም ብዙ ናቸው ። በአንድ በተወሰነ ጊዜ በዚህ ነገር ውስጥ እንደዋና ተብሎ የሚቆጠር ሌሎች ደግሞ በአጫፋሪነት ደረጃ የሚገኙ ቅራኔዎች አሉ ። ዋና የተባለው ቅራኔ ሲፈታ ለእነሱም መፍትሔ መንገድ ተጠረገ ማለት

ነው ። ለምሳሌ በኅብረተሰብ ውስጥ ዋናው ቅራኔ በበዝባዥና በተበዝባዥ መደቦች መሀከል ያለው ነው ። እሱ ሲፈታ ሌሎች በብሔረሰቦች ፣ በጾታዎች... መሀከል ያሉት መለስተኛ ቅራኔዎች አብረው ይፈታሉ ። ተቃራኒዎች ታግለው ለውጥን የሚያመጡትስ እንዴት ነው ? ይህንን ደግሞ ሁለተኛው የዲያሌክቲክስ ሕግ ይመልሰዋል ።

## ፪ኛ ፤ ከብዛት ወደዓይነት የመለወጥ ሕግ

ከብዛት የተነሣ ዓይነቱ ይለወጣል ግን ጠለቅ ብለን ከማየታችን በፊት ብዛትና ዓይነቱ ስንል ምን ማለታችን እንደሆነ እናብራራ ።

በአካባቢያችን ብዙ ነገሮችን እናያለን ። ግን ሁሉንም እምታችንን እንደ አንድ ነገር አርገን አናቀርባቸውም ። እየለየን እየለየን እንጠቁማቸዋለን እንጂ እንዲያው ዝም ብለው እንደ አንዳች ነገር ብቻ ብለው ተደበላልቀው አይታዩንም ። መጽሐፍ ጨርሶ « ብቻ » ከላሉብን በስተቀር ሽሚዙን ከድንጋይ ፣ ቤቱን ከጨረቃ ፣ ፈረሱን ከባሕርዛፍ የምንለይበት እነዚህ ሁሉ ነገሮች የራሳቸው የሆነ መታወቂያ አላቸው ። ይህ ማለት ዓይነታቸው የተለያየ ነው ። ዓይነት አንድ ነገር ከሌሎች በአካባቢው ካሉ ነገሮች የሚለየውን የሀልውናውን ምልክቶች አቀነባብሮ ይይዛል ።

ግን አንድ ነገር ሀልውናው ተለይቶ የሚታወቀው በዓይነቱ ብቻ አይደለም ። እርግጥ ማንኛውም ነገር የተወሰነ ዓይነት አለው ። ግን ብዛትም ( ቁመቱ ፣ ስፋቱ ፣ ክብደቱ . . . ቀጥሩ ፣ ሙቀቱ ቅዝቃዜው . . . ) የዚያኑ ያህል የተወሰነ ነው ። ምሳሌ

ማንኛውም ነገር የተለየ መልኩን እንደያዘ የሚቆየው በዓይነቱ ብቻ ሳይሆን በብዛቱም የተወሰነለትን ልክ ካላለፈ ብቻ ነው ። ብዛቱ እጅግ ተለውጦ ከዚህ ከልኩ ካለፈ ዓይነቱም ይለወጣል ማለት ነው ። ለምሳሌ ውኃን እንውሰድ ። ውኃ ከሌሎች ነገሮች ተለይቶ ዓይነቱን ጠብቆ የሚኖረው ብዛቱ ( እዚህ ላይ ብዛት የሚለው በተለይ ሙቀቱን ያመለክታል ) ሲያንስ በዝቅተኛው ዜሮ ድግሪና በዚያ በከፍተኛው ድግሪ ፻፬ መሀከል እስከተንሸራሸረ ብቻ ነው ። ከዚህ ውኃ ውኃ ሆኖ ከሚቆይበት ልክ ከተላለፈ ውኃው ውኃ መሆኑን ከመተው በስተቀር ወደሌላ ነገር ወደሌላ ዓይነት ነገር ይለወጣል ። እንፋሎት ይሆናል ። ወይ በረዶ ይሆናል ። ብዛት መለወጥ ፣ ከልክ ማለፍ የተነሣ ዓይነት ይለወጣል ማለት ነው ።

ውኃን ዘለዓለሙን አይተንም ። እንግዲህ በቀላሉ ለማየት እንደሚቻለው የአንድ ነገር ህልውና በተዋሐዱ ብዛትና ዓይነት ክልል ውስጥ የተወሰነ ነው ። ብዛትና ዓይነት እጅግ የተያያዙ በመሆናቸው ብዛት እየተለወጠ ቆሞ መቅረት አይቻልም ። ሲበዛበት ከልክ ሲታለፍ ዓይነትም ብዛትን ተከትሎ ይለወጣል ።

ይህ ከብዛት የተነሣ ዓይነት መለወጥ የማንኛውም ነገር እንቅስቃሴ የሚካሄድበት አጠቃላይ ሕግ ነው ። ዝቅ ብለን በኅብረተሰብ ውስጥ የሚደረጉ አብዮቶች የሚገለጡት በዚህ እንደሆነ እናያለን ። እንግዲህ ሌላ የሚጨመር ነገር ቢኖር ብዛትና ዓይነት ራሳቸው እንዴት እንደሚለዋወጡ መጠቆም ነው ። ብዛት የሚለዋወጠው ቀስ በቀስ ነው ። ሙቀት ክብደት ፣ ቁመት . . . ቀስ በቀስ ይጨምራሉ ይቀንሳሉ ። የአንድ ነገር ዓይነት ሲለወጥ ግን ከዚያኛው ጋር ሲነጻጸር « ከመቅጽበት » ከአንድ ዓይነት ነገር ወደሌላ በመዝለል ነው ማለት ይቻላል እንግዲህ ይህ ከመቅጽበት መዝለል ወዲያት ለመድረስ ነው ብሎ መጠየቅ ያስፈልጋል ። ለመሆኑ ለውጥ ለውጥ ተብሎ ግን የመላው ቁስ አካል እንቅስቃሴ የሚከተለው አቅጣጫ አለው ወይ ? አዎን አለው ። ይህንን ደግሞ እንማርክስ « የሻረ ሽረት » በሚባለው የዲያሌክቲክስ ሦስተኛ » ሕግ ይመልሱታል ።



## ፫ኛ ፤ የሻረ ሽረት ሕግ

በአካባቢያችን በየጊዜው እንደምናየው የቆየው እያረጀና እየተሻረ ሰርክ አዲስ ነገር ይፈጠራል ። አሮጌው በአዲስ መተካቱ ወይንም መሻሩ ነው ። ማንኛውንም ነገር ልብ ብለን ብናየው መወለድ ፣ ማደግ ፣ ማርጀት ፣ መሞት እንደሚያጋጥመው ለማየት ቀላል ነው ። ሽረት ብለን የምንጠራው ይህንን ነው ግን ይህ አሮጌውን ሽሮ የመጣው ዘለዓለሙን « አዲስ » « ወጣት » « ታዳጊ» ሆኖ አይኖርም ። በተራው ያረጃል ፣ ይደከማል ይሻራል ። ይህ ደግሞ ያለማቋረጥ ለዘለዓለም የሚካሔድ ነገር ነው ። እንግዲህ የሻረ ሽረት የሚባለው ሕግ ይህንን የማያቋርጥ ሹም ሽር ለመመልከትና ለመረዳት የሚጠቅም ሕግ ነው ማለት ነው ።

ይህ የማያቋርጥ ሹም ሽር የሚጓዝበት አቅጣጫ አለው ወይ ? አለው ። ይህንን ለማስረዳትና የሻረ ሽረትን ሕግ ለማሳየት ማርክሳስቶች ብዙውን ጊዜ ወደሚጠቁሟት የስንዴ ዘር እንሂድ ። አንድ ገበሬ ስንዴ ይዘራል ። ይች ስንዴ መሬት ውስጥ ትበሰብሳለች ። ተሻረች ማለት ነው ። ግን በሷ ቦታ የተዘራው ያብባል ። ሻሪው አበባው መሆኑ ነው ። አብቦ ፍሬ መስጠት አለና በምርት ጊዜ ያቺ በቀድሞ የተሻረችው ዘር ሃያ ጊዜ እጥፍ ሆና ትመጣለች ። ይህንን በሚያደርግበት ጊዜ ሻሪው አበባ ራሱ ይሻራል ። ፍሬ ሰጥቶ (አስበው) ይረግፋል ይሞታል ። ሻሪው ተሻረ ማለት ነው ።

እንግዲህ ከዚህ ተነስተን መልሰን ሌላ ዘር አገኘን ። ልብ ያላለ ሰው ዘር በዘር ተተካ ። የተለወጠ ነገር የለም ። ያለው የነበረው ተደጋገመ ይል ይሆናል ። ግን አይደለም ። መጀመሪያ የተነሣነው በአንዲት ዘር ነው ። ዞረን ስንገጥም በእጃችን ላይ ያለው ብዙ ዘር ነው ። ይህ መደጋገም አይደለም ። ማምረት ነው እንጂ ።

እንደዚህም ስለሆነ የሻረ ሽረት ሕግ የሚሰጠን አንድ መሠረታዊ አስተሳሰብ አለ ። እንዲህ ዓይነቱ ሹም ሽር በሚደረግበት ጊዜ እያንዳንዱ ከፍተኛ የእድገት ደረጃ ከሱ በፊት የነበረውን የሚሽረው ወደሌላ አሁንም ከፍተኛ ወደሆነ ነገር ለመለወጥ ሲሆን ይህንንም በሚያደርግበት ጊዜ አዲሱ ከአሮጌው ጠቃሚ የሆነውን ሁሉ አቅፎ በመጠበቅና በማዳበርም የሚደረግ ርምጃ ነው ማለት ነው ።

እንግዲህ ይህ የሻረ ሽረት ሕግ የማንኛውም የሰውም አቅጣጫ ከቀላሉ ወደተወሳሰበው ፣ ከዝቅተኛ ወደ ከፍተኛ የሚደረግ የማያቋርጥ የወደፊት ርምጃ ነው ማለት ነው ። ይህ በጠቅላላው የተፈጥሮ እድገት ብቻ ሳይሆን የሰዎችም ታሪክ የሚከተለው አቅጣጫ ነው ። የታሪክ ርምጃ ወደፊት ነው ። ይህ መሠረታዊ እምነት ነው የማርክስን ተከታዮች ስለወደፊቱ የሰው ዘር ዕድል እጅግ ተስፋ የሚሰጣቸው ። በዚህ በማመን ነው የሰው ልጅ የወደፊት ዕድል ከፀሐይ ደምቆ የሚታየው ። ለዚህ ነው አብዮታውያን « ትናንት መጥፎ ነበር ፣ ዛሬ ደህና ነው ነገ ደግሞ ይሻላል» የሚል አነጋገር ያለባቸው ። በሌላ በኩል ግን አድኃሪዎች ሁልጊዜ ጉዟችን «ወደከፉ ቀን » ይመስላቸዋል ። ለምሳሌ ማንኛውም ነገር ወደፊት መራ

መዱን የዘነጋ አድኃሪ አስተሳሰብ « ሲያልቅ አያምር » በሚል ይገለጻል ። አድኃሪዎች የወደፊቱን በተስፋ እንደማተኮር ያለፈውን በናፍቆት ይመለከታሉ ። « ዛሬ ምን አለና » « ዱሮ ቀረ !» « ምን አለ የዛሬ ሰው » የሚሉት ሁሉ አድኃሪ ፍልስፍና የሚከተሉ ሰዎች ስለታሪክ ስለኅብረተሰብ የወደፊት ዕድል ያላቸውን የጨለመ አስተሳሰብ የሚያበስር ነው ።

ይህንንም ስላልን ታሪክ ሁልጊዜ ወደፊት ይራመዳል ስላልን ወጣ ውረድ የለበትም ፤ ሳይገታ ሳይቀለበስ ያለማቋረጥ ወደፊት ይቀጥላል ማለት አይደለም ። በጠቅላላ አቅጣጫው ሲታይ ወደፊት ነው ቢባል ም አልፎ አልፎ ለተወሰነ ጊዜ የመቀልበስ አደጋ ሊያጋጥመው እንደሚችል መዘንጋት ዞሮ ዞሮ የሕዝብ ወገን ማሸነፉ አይቀርምና እጅን አጥፎ ድልን መጠበቅ ይቻላል የሚል ክትግል የሚያዘናና አቋም ላይ ሊጥለን ይችላል።ግን እንግዲህ ይህን ሁሉ ጠለቅ ብለን ለመረዳት የማርክስ ፍልስፍና ሌላ ክፍል ወደሆነው ወደ ታሪክ ቁስአካልነት እንግባ ።

ማርክስ ኅብረተሰብን ከጠቅላላው ቁስአካል ውጭ አይመለከተውም ። ስለዚህ ኅብረተሰብ የሚያጠኑው ቁስአካላዊ በሆነ ዓይን ሲሆን ታሪክን ሲያጠና ከላይ በጠቀስናቸው የዲያሌክቲክስ የለውጥ ሕግጋት እንደተጠቀመ ነው ። ማርክስ ስለ ኅብረተሰብ ያለው ፍልስፍና የታሪክ ቁስአካልነት የተባለው ለዚህ ነው ።

(ይቀጥላል ።)